# ምዕራፍ አራት

## መስመራዊ የእኩልነት አረፍተ ነገሮች

ከዚህ በታች ለተሰጡት መስመራዊ የእኩልነት ዓ/ነገሮች  የተለዋዋጭ ዋጋ ፍለጉ?

24 = 7 + ሸ    ሸ= ..........    15 + በ = 25  በ =……..    መ + 7 = - 16   መ = ………

ቀ – 8 = - 12   ቀ = ..........    ሸ – 13 = - 28   ሸ= ..........    100 = 25 x ሀ   ሀ = ..........

- 6 = $\frac{በ}{42}$   በ = ..........    - ሀ/9 = 3  ሀ = ..........    -15ለ = 0    ለ = ..........

21 = -3ቀ   ቀ = ..........    -126 = 14ከ   ከ = ..........    -16 + መ = -15   መ = ..........

-13 = ለ – 15   ለ = ..........    -6 + መ = 12   መ = ..........    -16 + ነ = - 9    ነ = ..........

የ – 5 = 17   የ = ..........    ፐ – 8 = - 5  ፐ = ..........    14በ = -56    በ = ..........

-17ረ = -204    ረ = ..........    -143 = -11ተ    ተ = ..........    -5 = ቸ/18    ቸ = ..........

LIVEWORKSHEETS

# መስመራዊ የእኩልነት ዓ/ነገሮች  የቃላት ጥያቄዎች

1. ሚኪ ከአንድ ሱቅ በ 29 ብር ኮፍያ ገዛ፡፡ ለባለሱቁ 100 ብር ቢሰጠው ሚኪ ስንት ብር መልስ ይኖረዋል?

2. እናቴ እቤት ውስጥ ኩኪስ ለመስራት 9 ኩባያ ዱቄት ያስፈልጋታል ፡፡ እቤት ውስጥ ያላት 3 ኩባያ ዱቄት ብቻ ቢሆን እናቴ ስንት ኩባያ ተጨማሪ ዱቄት ያስፈልጋታል?

3. አባቴ ከ 6 አመት በፊት እድሜው 60 ቢሆን አሁን ያለው የአባቴ እድሜ ስንት ነው?

4. ሳምሪ ለልደቷ አክስቷ 14 ብር ሰጠቻት ፡፡ አሁን ሳምሪ 53 ብር አላት ፡፡ ሳምሪ መጀመሪያ ስንት ብር ነበራት?

5. ከ 19 ዓመት በኋላ አጎቴ 37 ዓመት ይሆነዋል ፡፡ አሁን አጎቴ እድሜው ስንት ነው ?

6. ባለፈው ሳምንት ሄኖክ 10 ኪሊሜትር ከ ናቲ ያነሰ ርቀት ሮጧል ፡፡ ሄኖክ የሮጠው ርቀት 11 ኪሎሜትር ቢሆን ናቲ የሮጠው ርቀት ምን ያህል ነበር ?

7. አንድ ቂጣ ለመጋገር 3 ኩባያ ዱቄት ያስፈልጋል ፡፡ በስህተት 9 ኩባያ ዱቄት ቢጨመር ምን ያህል የማያስፈልግ ዱቄት ተጨምሯል ?

8. ናታን የተለያዩ  ዘጠኝ እስክርቢቶዎችን ለመግዛት 36 ብር ከፈለ ፡፡ የእያንዳንዱ እስክርቢቶ ዋጋ ምን ያህል ነው ?

9. ሜቲ እና ሳሮን ከትምህርትቤት ወደቤታቸው ሲሄዱ መሬት ላይ የወደቀ ብር አገኙ ፡፡ ያገኙትን ገንዘብ እኩል እኩል ሲካፈሉ እያንዳንዳቸው 11 ብር ደረሳቸው፡፡ እነሜቲ መሬት ላይ ወድቆ ያገኙት ገንዘብ ምን ያህል ነው ?

LIVEWORKSHEETS

10. ሃና የተለያዩ የታሸጉ ቸኮሌቶችን በ 21 ብር ገዛች ፡፡ የአንድ እሽግ ቸኮሌት ዋጋ 3 ብር ቢሆን ሃና ስንት እሽግ ቸኮሌቶችን ገዝታለች?

11. አራት ሰራትኞች በእርሻ ላይ ቡና ለመልቀም ተቀጥረዋል ፡፡ እያንዳንዱ ሰራተኛ 7 ሜ በ 8 ሜ ስፋት ያለው መሬት ቢመደብለት ጠቅላላ ቡና የሚለቀምበት የእርሻ መሬት ስፋት ምን ያህል ይሆናል ?

12. አንድ እሽግ ሶፍት ዋጋ 5 ብር ቢሆን በ 30 ብር ስንት እሽግ ሶፍት መግዛት ይቻላል?

13. ማርታ እና ዘጠኝ ጓደኞቿ በ አንድ ሬቶራንት ውስጥ በጋራ ምሳ ከበሉ በኋላ የመጣዉን ሂሳብ ለእያንዳንዳቸው ሲከፈል 13 ብር ይደርስባቸዋል ፡፡ የምግቡ ዋጋ ምን ያህል ነው?

LIVEWORKSHEETS